ኢትዮ ቻናል
የምንፈራው ውሸትን ብቻ ነው!!

# የመድረክ ማኒፌስቶ በድጋሚ አጨቃጫቂ ሆነ

## “3000 ዘመን የሚባለው የኢትዮጵያ ታሪክ ከየት የመጣ እንደሆነ አናውቀውም”

አቶ ቡልቻ ደመቅሳ

የመድረክ አባላት ማኒፌስቶውን ለማየት ማክሰኞ ሰኔ 9 ቀን 2001 ለሁለተኛ ጊዜ 5ኪሎ በሚገኘው የደቡብ ህብረት ጽ/ቤት መሰብሰባቸው ታወቀ። ቅርበት ያላቸው ምንጮች በተለይ ለኢትዮቻናል እንደገለፁት በማክሰኞው ስብሰባ በኦፌድን ተወካዮች በቀረቡ ሁለት ጉዳዮች የተነሳ በድጋሚ ከፍተኛ አለመግባባት ሊፈጠር ችሏል።

የመጀመሪያው ለአለመግባባቱ ምክንያት የሆነው ሃሳብ የቀረበው በአቶ ቡልቻ ደመቅሳ እንደነበር ምንጮቻችን ይናገራሉ። አቶ ቡልቻ በማኒፌስቶ ገፅ 4 ላይ 3ተኛ አንቀፅ የተዘረዘረው ፈፅሞ እንዲሰረዝ ጠይቀው ነበር። የኢትዮ-ቻናል ምንጮች እንዳሉት አቶ ቡልቻ በሶስተኛው አንቀፅ የሰፈረውን በማጣቀስ “ኢትዮጵያ ስለሚለው ታሪክ ጠቅላላ የኦሮሞ ህዝብ አያውቀውም” ብለዋል። ጨምረውም “3000 ዘመን ታሪክ የሚባለውም የምን ታሪክ እንደሆነ አናውቀውም” “ከየት እንዳመጣችሁት አናውቅም” ሲሉ ጠንከር ያለ ሃሳብ መሰንዘራቸውን ምንጮቻችን ገልፀውልናል።

ለማክሰኞው የመድረክ ስብሰባ ቅርበት የነበራቸው የኢትዮ-ቻናል ምንጮች እንደነገሩን አቶ ቡልቻ በማኒፌስቶው ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ የሚገለፅው መሰረዝ እንዳለበት ሃሳብ ሲያቀርቡ በስሜት ተውጠው ነበር። ለተሰብሳቢዎቹ ሃሳባቸውን ሲያብራሩ “የአድዋን ጦርነት ሆነ ድሉን የኦሮሞ ህዝብ አያውቀውም፡ አልተሳተፈበትምም” ማለታቸውን ምንጮቻችን ገልፀውልናል። በሌላም በኩል ከዚሁ ፓርቲ ከኦፌድን ተወክለው በስብሰባው የተገኙት ዶ/ር ሞጋ በበኩላቸው “ኢትዮጵያ የአፍሪካ ተምሳሌት አይደለችም” የሚል አቋማቸውን አንፀባርቀው ነበር። እንደ ምንጮቻችን ከሆነ ዶ/ር ሞጋ አቋማቸውን ሲያብራሩ “ላንትና እነዚህን አፍሪካውያን ባሪያ ትሏቸው አልነበረም ወይ? ኢትዮጵያ የአፍሪካ ህብረት እንብርት ናት የምትሉትን የኦሮሞ ህዝቦች አናውቀውም ካሉ በኋላ በማኒፌስቶው የተጠቀሰው እንዲሰረዝ ጠይቀዋል።

የኦፌዴን ተወካዮች ሌላ ያቀረቡት ተቃውሞ በማኒፌስቶው ገፅ 23 አንቀፅ 6/6.7 የተገለፀው ላይ ነበር። በዚህ አንቀፅ “ከአማርኛ በተጨማሪ በበርካታ ህዝብ የሚነገር ሌላ ቋንቋ የፌደራሉ መንግስት የስራ ቋንቋ እንዲሆን ይደረጋል” የሚል ሃሳብ ሰፍሮ ይገኛል። ይሁን እንጂ የኦፌዴን ተወካዮች አንቀፁ ክፍተት እንዳለበት በመግለፅ ማኒፌስቶውን መቃወማቸውን ምንጮቻችን አስረድተውናል። “የኦሮምኛ ቋንቋ የመንግስት የስራ ቋንቋ ይሆናል ተብሎ ሊፃፍ ይገባል” ይላሉ ተወካዮቹ።

የተገለፁት ሁለት ሃሳቦች የስብሰባውን ተካፋዮች ከፍተኛ ስሜት ውስጥ ያስገቡና ጭቅጭቅ የፈጠሩ ሆነው መገኘታቸውን የኢትዮ-ቻናል ምንጮች ይናገራሉ። በጉዳዩ ዙርያም በእለቱ የተገኙ የፓርቲው አመራሮች የተለያዩ የተቃውሞ ሃሳቦችን አቅርበው ንትርክም እንድተከሰተ ለመረዳት ችለናል።

በመጨረሻም በማኒፌስቶ ዝግጅት ወቅት ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው የተለያዩ ሃሳቦች የቀረቡ ቢሆንም አቶ በቀለ ጅራታ በእለቱ በሰጡት አስተያየት “አሁን በጣም ግራ የሚያጋባና መድረክን ሊፈታተን የሚችል ሃሳብ መምጣቱ ጥሩ አይደለም” ብለዋል። በማኒፌስቶው መግቢያ ያለውን አንቀፅ “አባባሉን የማረም ሂደት” እንዲፈፀምበት አብዛኛዎቹ ተሰብሳቢዎች እንደተስማሙበት ምንጮቻችን ያስረዳሉ፡ ይሁንና “ኦሮምኛ የመንግስት ሁለተና የስራ ቋንቋ ይሆናል” የሚለው ተቀባይነት ሊያገኝ አልቻለም። ሃሳቡን በውስጠ ታዋቂነት ኣአስቀምጦ ለማለፍ ግን ተስማምተዋል። ቢሆንም አንዳንድ የስብሰባው ተሳታፊዎች “በዚህ አይነት እንዴት መቀጠል እንችላለን?” የሚል ስጋት አድሮባቸዋል። እነዚህ ስጋት ውስጥ የገቡ ተሰብሳቢዎች “እነዚህ ሰዎች የኦነግን ሃሳብ እንዳለ እንዲፈፀም እየፈለጉ ነው” በሚል ግራ እንደተጋቡ ምንጮቻችን ተናግረዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የመድረክ አመራር አባላት የሚያደርጉት ስብሰባ ምስጢር እይወጣ ለተለያዩ ጋዜጦች እየተሰጠ መሆኑን በተመለከተ በስብሰባው ማሳሰብያ ተሰጥቶበታል። እያንዳንዱ የፓርቲ አመራር ራሱን መጠበቅ እንዳለበት በማሳሰብያ መልክ እንደተነገረ የኢትዮ-ቻናል ቅርበት ያላቸው ምንጮች አስረድተዋል። ይሄ ምስጢር የማውጣቱ ችግር በተለይ አንዳንድ ፓርቲዎች ወደ መጨረሻ አካባቢ መድረኩን ከተቀላቀሉ በኋላ የተፈጠረ መሆኑ መገለፁንም ለመረዳት ችለናል።